# ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በረዥም የታሪክ ጉዞዋ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በእኩልነት ደረጃ ስታገለግል የኖረች እናት ቤተ ክርስቲያን ናት አሁንም አገልግሎቷን ከመፈጸም የተገታችበት ጊዜ የለም፤

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሀገር ብትሆንም ሕዝቦቿ በሃይማኖት፣ በጎሣና በቋንቋ ሳይለያይዩሀገርን የሚወር፤ ነፃነትን የሚገፍ ጠላት በሀገር ላይ ሲነሣ አንድነቱን አጠናክሮ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ደሙን አፍሶ አጥንቱን ከስክሶ የሀገሩን ነፃነት ሲያስከብር ኖሮአል።

በተለይም የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች በወንድማማችነት ተሳስበው የኖሩት አንዱ የሌላውን እምነትና ሥርዓት ሳይነካ ከኢትዮጵያዊነት ስሜት በመነጨ መተሳሰብና ዕውነተኛ ፍቅር ነው ።

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሕግና መንግሥት ባለበት ሀገር በአንዳንድ የክልልና የዞን መስተዳድሮች በባሌ ጎባ፣ በጣና በለስ፣ በኦሮምያ ክልል፣ አሁን ሰሞኑን ደግሞ በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልልና በአንዳንድ ቦታዎች በተለያየ ምክንያት በሚፈጠር የእርስ በርስ ግጭት መነሻነት በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ፣ በቅዱስ ረድኤቱ የከበረ፣ ሕያዊት፣ ነባቢት ነፍስ የተዋሐደችው፣ ፍጹም አእምሮና ዕውቀት የተሰጠው የሰው ነፍስ እየጠፋ እናያለን፤ ይልቁንም በሱማሌ ክልል አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤ ካህናት ተገድለዋል፤ ንብረት ተዘርፎአል፡፤

ዛሬ በመላ ሀገራችን ከመሐል ኢትዮጵያ እስከጠረፍ ዳርቻ ባሉት ክልሎችና የመስተዳድር ዞኖች ሰላም፣ ፍቅር አንድነት መከባበርና መቻቻል፤ እየተደማመጡና እየተናበቡ መሥራት በበለጠ እንዲዳብርና እንዲሰፍን የአመራር መርሕ በስፋትና በጥልቀት እየተሰጠ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ ለሚተላለፈው መመሪያና የሰላም መልእክት ትኩረት ባለመስጠት የሀገርና የወገን ፍቅር ስሜት የተለየው የጭካኔ ሥራን መሥራት ከኢትዮጵያውያን ዜጎች የሚጠበቅ ተግባር ሆኖ አላገኘነውም።

ይህ መወገዝ ያለበት የዓመፅ ተግባር አብረው በኖሩ ወንድማማቾች መካከል የፈጠረው ግጭት፤ አለመግባባትና መቃቃር በዚህ ሳቢያ እየተካሔደ ያለው መጠፋፋት እየሰፋና እያደገ ወደሌላ ከመሸጋገሩ በፊት ከወዲሁ ታስቦበት ተፋጥኖ ይገታ ዘንድ የባለ ድርሻ አካላት ሁሉ መረባረብ ይጠበቅባቸዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የተፈጠረው ችግር ተወግዶ የተሟላ ሰላምና መረጋጋት ዕውን እስከሚሆን ድረስ የመፍትሔው አካል በመሆን የሚቻላትን ሁሉ በመፈጸምና በማስፈጸም ያለባትን ሀገራዊ ግዴታና ኃላፊነት በተግባር ማረጋገጥ ይጠበቅባታል።

የሀገሪቱንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ሰላምና መረጋጋት በሚጎዳ መንገድ የሚሔዱ ግለሰቦች ሁሉ እንዲስተካከሉ ከእግዚአብሔር ሕግ አኳያ ምክርና ትምህርት በመለገስና በማስተላለፍ ዓላማዋና ዓይነተኛው ተግባርዋ እንደሆነም ማስገንዘብ ይኖርባታል ።

ስለዚህ ሰላምና መረጋጋት የሚመነጨው ከቤተ ሰብና ኅብረተሰ ሰብ ስለሆነ፤
ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲመክሩ፣ እንዲገሥፁ እንዲያስተምሩ ያስፈልጋል ።

- ኅብረተሰቡም በዘር በሃይማኖትና በጎሣ ሳይለያይ በሀገራችን በአንዳንድ አካባቢ እየተሰማና እየታየ ካለው መጥፎ እንቅስቃሴ ራሱን እንዲገታ እንዲቆጣጠር፤
- ካህናትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም የመልካም ስነ ምግባር መሠረት በሆነችው ሀገራችን ላይ ችግሩ በተከሰተበት አካባቢ እየተገኙ ትምህርተ ወንጌል እየሰጡ የማረጋጋት፣ የማጽናናትና የማስታረቅ ሥራን እንዲሠሩ።
- ይህን አላስፈላጊ ግጭት ከሕዝባችንና ከሀገራችን እግዚአብሔር እንዲያርቅልን ጾመ ፍልሰታ ለማርያምን ምክንያት በማድረግ ሙሉ ሰባኤውን በሁሉም ገዳማትና አድባራት ጸሎተ ምሕላ እንዲደረግ፤
- በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል በጅጅጋ፣ በጎዴ ከተማና በሌሎችም ከተሞች በደረሰው አሰቃቂ ግድያና ዘረፋ ምክንያት በየመጠለያው በረሀብ፣ በጽምና በእርዛት ለሚሰቃዩ ካህናትና ምእመናን መንግሥት ተፋጥኖ እንዲደርስላቸውና የነፍስ አድን ሥራ እንዲሠራ በአጽንኦት እናሳስባለን ።
- ለሞቱት ወገኖቻችንም በመላ ገዳማትና አድባራት ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ፤
- በችግሩ ዙሪያ የሚገኙ የክልልና የዞን መስተዳድር አካላትም የገላጋይ ያለህ የሚል ሮሮ እስከሚሰማ ድረስ ሳይጠብቁ በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠውን ድንጋጌ በማክበርና በማስከበር ከመንግሥትና ከሕዝብ የተረከቡትን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጡ በቤተ ክርስቲያናችን ስም አደራ እያለን ይህን መልእክት እናስተላልፋለን ።

ሕልፈተ ሕይወት ያጋጠማቸው ወገኖቻችንን እግዚብሔር በመንግሥቱ እንዲቀበልልን ያዘኑትን እንዲያረጋጋልን፤ የተጎዱትን በምሕረቱ እንዲጎበኝልን፤ ዘላቂ ሰላምም እንዲሰጠን እንጸልያለን ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አባ ማትያስ ቀዳማዊ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱመም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት